# የጋራ ውይይት/ ጥያቄዎችና መልሶች

**የውይይቱ አባላት፡** አቶ ደሳለኝ፣ፓ/ር ግዛቱ፣ዶ/ር አንደርሰን እና አቶ ፓ/ር ዘውዱ

1. ግጭት ምንድነው? <u>ዶ/ር አንደርሰን</u>
   ሀ. አለመስማማት
   ለ. በግጭት ምክንያት የስልጣን ሽኩቻ፣በስልጣን ያላአግባብ መጠቀም
   ሐ. አንዱ ሌላውን በስህተት መረዳት
2. ባለንበት አለም ግጭት የማይቀር እውኔታ የሆነው ለምንድነው? <u>ዘውዱ</u>
   ሀ. ግጭት በቤተሰብ መካከል፣ግጭት ከጎረቤት ወይም ከማህበረሰብ ጋር፣ግጭት በሥራ ቦታና በቤተክርስቲያን
   ለ. እኛ ሰዎች እንደመሆናችን የተለያዩ አስተሳሰብና አመለካከት አለን፡፡
   ሐ. ራስ ወዳዶች ነን፡፡
3. ለግጭት እንዴት ምላሽ እንሰጣለን? <u>ደሳለኝ</u>
   ሀ. አንዳንድ ሰዎች ግጭገት ሲከሰት ይዘጋሉ፤ያኮርፋሉ፤ለመሸሽ ይሞክራሉ፡፡
   ለ. የተፈጠረውን ግጭት ለሌሎች እንናገራለን፤ ሌሎችን እናማለን፤ሌሎችንም ወደ እኛ ሀሳብ እንዲመጡ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡
   ሐ. ውይይት ማድረግ
   መ. አማላጅ (ስሞታ መንገር)
4. ግጭት ሲከሰት ከግጭቱ ለመሸሽ ለምን እንሞክራለን? <u>ዘውዱ</u>
   ሀ. ፍርሃት
   ለ. የባሰ መጎዳት ሊያመጣ ይችላል፡፡
   ሐ. ተስፋ መቁረጥ
   መ. ለግጭቱ መፍተሄ ለማምጣት ጉልበታችንን እንጠቀማለን፡፡ ( ይህ ምን ያመጣል?)
   ሠ. እኛም የግጭቱ አካል መሆናችንን አለማመን
   ረ. ግጭትን አንወድም (በባሰ ግጭት ውስጥ አትክተተኝ ማለት ነው)፡፡
5. አንድ ሰው የበላይ ቢሆን ምን ይሆናል? አንድ ሰው መፍተሄ መፈለጉን ትቶ ቢሸሽ ምን ይሆናል? <u>ግዛቱ</u>
   ሀ. በዚህ ጊዜ ግጭቱ መፍተሄ አያገኝም፡፡ ምሳሌ ስጥ፡፡
6. ግጭት ሌሎችን የሚጎዳው እንዴት ነው? <u>ዶ/ር አንደርሰን</u>
   ሀ. መራርነት
   ለ. ቁጣ
   ሐ. በሽታ
   መ. የአእምሮ ሰላም ማጣት
   ሠ. በመንፈሳዊ ሕይወት መድከም
   ረ. አንድነትን ማጣት
   ሰ. ለሰይጣን ክፍተት ይሰጣል
   ሸ. ጥሩ ሥራ እንዳይሰራ ያደርጋል
   ቀ. ጤናማ ግንኙነት እንዳይኖር ያደርጋል
   በ. በቤተሰብ ውስጥ ደስታ እንዳይኖር ያደርጋል
   ተ.በሥራ ቦታ ደስታ እንዳይኖር ያደርጋል
7. የዚህ ሥልጠና ግቡ ምንድነው? <u>ዶ/ር አንደርሰን</u>
   ሀ. ግጭትን ማስወገድ፣ሰላምና ሕብረት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

ለ. ግጭትን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በቂ ክህሎት እንዲኖር ለመርዳት ነው፡፡
ሐ. አንድነት እንዲጠነክር ማድረግ ነው፡፡
መ. ጤናማ ሕብረት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

8. በግጭት ጊዜ በጣም ብትቆጣ ምን ማድረግ አለብህ? ዘውዱ
    ሀ. በረጅሙ መተንፈስ፦ በስሜት ውስጥ ከገባህ በረጅሙ ተንፍስ፤ራስህንም አረጋጋ፡፡
    ለ. የሚያስቆጣ ሁኔታ ሲፈጠር ወጣ ብሎ መሄድ፦ መታገስ
    ሐ. ይቅር ለማለት ዝግጁ ሁን፤በቁጣህም ላይ ፀሐይ አይጥለቅ፡፡

9. ግጭትን ለማስወገድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ዘዴዎች ምንድናቸው? ግዛቱ
    ሀ. በጥሞና ማዳመጥ
    ለ. ትሁት ልቦና፦ ምናልባት ስህተቱ የእኔ ሊሆን ይችላል ማለት
    ሐ. የእግዚአብሔርን ምክር መስማት፦ ባለጉዳዩን ሰው ይቅር ስለ እግዚአብሔር ማለት
    መ. በቁጣህ ላይ ፀሐይ አይጥለቅ (ቁጣህን በውስጥህ ለረጅም ሰዓት አታቆይ ማለት ነው)፡፡

10. ጥሩ አዳማጭ እንድንሆን የሚያደርገን ምንድነው? ዘውዱ
    ሀ. ብዙ ከመናገር ማዳመጥ
    ለ. ነገሮችን በስሜት ከማየት ይልቅ ሌላው ሰው ለመናገር የፈለገውን ነገር በትኩረት ማዳመጥ
    ሐ. አንድ ሰው ሲናገር ሌላ ቦታ ከማየት ዓይኑን ማየት
    መ. ውስጥህን ከፍተህ በትህትና አድምጥ፡፡ ምናልባት ተሳስቼ ይሆን? ብለህ ራስህን ጠይቅ

11. ስለ ግጭት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
    መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገር ይናገራል፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት ባለህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ በግጭት ዙሪያ የተጻፈ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ታያለህ፡፡
    ሀ. ዛሬ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሰላምንና አንድነትን እንደሚፈልግ አስታውስ፡፡
    ለ. የሰይጣን ፍላጎት በሰዎች መካከል መከፋፈል እንዲኖርና ችግር እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡

***ማጠቃለያ ሀሳብ፦ ያዕቆ፡1***
***ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ***
***ለመናገርም የዘገየ***
***ለቁጣም የዘገየ ይሁን***

በሚቀጥለው ሳምንት፦
ዛሬ ከተማርከው ነገር ተነስተህ በሚመጣው ሳምንት ምን ታደርጋለህ
በዚህ ሳምንት ግጭትን ማስወገድ በተመለከተ ምን እንዳደረጉ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች የራሳቸውን ተሞክሮ በሚቀጥለው ሮቡዕ እንዲያካፍሉ እንጠይቃለን፡፡

ሀ. አንተ በሕይወትህ ከሰው ጋር ተጋጭተህ ያንን ግጭት ለማቃለል የወሰድከው ርምጃ ካለ ተናገር፡፡
ለ. ግጭትን ለማስወገድ ሞክረህ አልሳካ ያለህ ጊዜ ካለ ተናገር፡፡

## ለመሪዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

1. ለቡድን ጥናት ጊዜ ራስህን እንዴት ታዘጋጃለህ?
2. ስለመርነት ያሉህ ጥያቄዎች ምንድናቸው?
3. ስትመራ ብርታት ይሰማሃል ወይስ ሞራል ታጣለህ?
4. ሌሎች በቡድኑ ውስጥ እንዲሳተፉ እንዴት ታደርጋለህ?
5. ለፀሎት በቂ ጊዜ አለ?
6. አንድ ሰው ቀሪ ቢሆን ምን ታደርጋለህ?
7. በሳምንቱ መካከል ለሁሉም አባል ትፀልያለህ?
8. በሳምንቱ መካከል ደውለህ ወይም በአካል ታገኛለህ?
9. ለቡድኑ አባላት የሚታካፍላቸው ሥራዎች አሉህ? ምንድናቸው?
10. በቡድን ጥናት ጊዜ ከበድ ያለ ጥያቄ ቢነሣ ምን ታደርጋለህ?
11. ለቡድንህ አባላት ግልጽ ነህ?
12. ለቡድንህ አባላት ምሳሌ ለመሆን የምታደርገው ምንድነው?
13. ቡድንህን ታስተምራለህ? ወይስ ትሰብካለህ? ወይስ በውይይቱ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ታመቻቻለህ?
14. ለቡድኑ ያስፈልጋሉ የምትላቸው ነገሮች አሉ? ለምሳሌ፡- ወንበር፣የመሰብሰቢያ ቦታ የመሳሰሉት።
15. በቡድንህ ውስጥ ግጭት ቢፈጠር እንዴት ታስወግዳለህ?
16. ሁል ጊዜ በጊዜና በቦታ ትገኛለህ?